King County

# HEARING EXAMINER GUIDE

## FOR-HIRE APPEALS

**Amharic**



**David Spohr, Hearing Examiner**
Metropolitan King County Council
hearingexaminer@kingcounty.gov
www.kingcounty.gov/independent/hearing-examiner

King County Courthouse
516 Third Avenue, Rm 1200
Seattle, Washington 98104
(206) 477-0860

# የችሎት መርማሪ መመሪያ ለቅጥር የመንጃ ፍቃድ ይግባኞች

## ይህ መምሪያ ምንድን ነው?

ይህ መመሪያ ለሹፌር ቅጥር ይግባኞች የችሎት መርማሪውን ሂደት አጠቃሎ ያቀርባል። ተራ ሰዎችን ለመርዳት የታሰበና ህጋዊ ክብደት የሌለው ነው። መርማሪው ጥያቄዎችን ያመጣል።

## ፈታኙ ማነው?

መርማሪው በኪንግ ካውንቲ መዝገቦችና የሙያ ፍቃድ ክፍሎች (RALS) ላይ የሹፌር ቅጥርን በተመለከተ ችሎቶችን ለማካሄድ የተሾመና ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ በኪንግ ካውንቲ ካውንስል የተሾመ ነው። መርማሪው እንደ ዳኛ ገለልተኛ ውሳኔ ሰጪ ነው። የመርማሪው ቢሮ ለካውንስሉ ነው የሚሰራው፤ለ RALS አይደለም።

## ስለ መገናኛ መንገድስ?

በ TDD ቁጥር በመደወል የምልክት ቋንቋ በነጻ ይገኛ (206) 296-1024።
ከኢንግሊዝኛ ውጪ ለሆኑ ቋንቋዎች አስተርጓሚ በነጻ ይገኛል። የመጓጓዣ ገደብ ላለባቸው በስልክ ለመሳተፍ የመሳሰሉ አማራጮችን ለማየት ለመርማሪው ይደውሉ። ይደውሉ। (206) 477-0860 ወይም ኢሜይል ያድርጉ hearingexaminer@kingcounty.gov። እባክዎ በሂደቱ ውስጥ ጥያቄዎችን ቀድመው ይጠይቁ።

## ይግባኞን እንዴት ይጀምራሉ?

የ RALSን ትእዛዝ የተቀበሉ ሰዎች ኪንግ ካውንቲ ስለ ክሱ የሚለውን መርማሪው እንዲሰማ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። የይግባኝ ክፍያ የለም፤ ንገር ግን የሚከተሉት ሶስት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው ፡-

1. **ሰአት፡-** ይግባኝዎን ለማስገባት ቀነ ገደቡ RALS ውሳኔውን *ካሳለፈ* በኋላ ባሉት 24 የስራ ቀናት ነው። RALS በራሱ ትእዛዝ በሚፈጽምበት ጊዜ በዛ ቀን ሰአቱ መቁጠር ይጀምራል። RALS ትእዛዙን ፖስታ በሚልክበት ጊዜ ሰአቱ መቁጠር የሚጀምረው እርስዎ በተቀበሉበት ቀን *ሳይሆን* RALS ኢሜይል በላከበት ቀን ነው።

2. **ማድረስ፡-** በቀነ ገደቡ የይግባኝ መግለጫዎን ለፖስታ ቤት ማቅረብ በራሱ በቂ *አይደለም*፡ RALS በመጨረሻው ቀን ይግባኝዎን ግዴታ *መቀበል* አለበት(ፖስታ ለማድረስ በአብዛኛው ብዙ ቀናት ይፈጃል)። በጊዜው ያልቀረበ ይግባኝ አይፈቀድም — የሚለወጥ ነገር የለም። ይህ አግባብነት ያለው ባይመስልም ነገር ግን ህግ ነው። ይግባኝዎን፡-
   - በፖስታ 201 S. Jackson Street, Suite 202, Seattle, WA, 98104 ላይ በአካል በመቅረብ ማስገባት ይችላሉ (የስራ ሰአቶችንያረጋግጡ https://kingcounty.gov/depts/records-licensing.aspx)፤
   - ኢሜይል ለመላክ KCFHInspector@kingcounty.gov (መድረሱን ለማረጋገጥ RALSን ይጠይቁ)፤ ወይም
   - ትክክለኛ ቅጂ ለመላክ (206) 296-4029።

3. **ይዘት፡-** የይግባኝ መግለጫዎ ማካተት ያለበት ነገሮች፡-
   a) ይግባኝ ያሉበትን የRALS ውሳኔ(ዎች) ኮፒ ወይም የRALSን የፋይል ቁጥር(ሮች) እና የውሳኔ ቀን(ናት)፤

b) በክሱ ላይ ያሎትን ፍላጎት ማብራሪያ (ለምሳሌ የመንጃ ፍቃድ ይፈልጋሉ)፣

c) RALS በውሳኔው ላይ ሰርቷል ብለው የሚያስቡትን ስህተት(ቶች) ("ጥሰቱ ተሰርዟል፤"ወይም "አነስ ባለ ጥቃት እንዲታይ እጠይቃለው፤" ወይም "_____ተፈጥሯል ግን_________," ወ.ዘ.ተ)፣

d) የRALS ውሳኔ(ዎች) መቀየር ("__________________________________________መንጃ ፍቃዴን የሚያሳጣ መሆን የለበትም፤"ወ.ዘ.ተ) ወይም መስተካከል("ቅጣቱ በጣም ከፍተኛ ነው፤"ወ.ዘ.ተ) አለበት ብለው የሚያስቡበትን ልዩ ምክንያት(ቶች) ፣

e) የRALS ውሳኔ(ዎች) እንዴት እንደሚጎዳዎት ወይም ሊጎዳዎት እንደሚችል ("ያለ መንጃ ፍቃድ እኔ__") እና

f) ምን አይነት ውጤት(ቶች) እንደሚፈልጉ ("ክህደቱ እንዲሻር" ወይም "ቅጣቱ እንዲቀነስ"ወ.ዘ.ተ)።

ይግባኝዎ ሁሉንም ማስረጃ(እንደ ሰነድ አይነት) ማካተት ባይጠበቅብዎትም ይግባኝዎን ለመደገፍ ማንሳት የሚፈልጉትን ሁሉንም ነገሮችና ጉዳዮች ያካተተ ይግባኝ ማስገባት ይችላሉ—ከላይ ያሉትን (c) እና (d)ን ይመልከቱ። በትክክል ምን ማለት እንደሚፈልጉ እርግጠኛ ካልሆኑ ምንም ያልተሟል ቢሆንም ይግባኝዎን በቀነ ገደቡ ለ RALS ማድረስዎን ያረጋግጡ።

የመጀምሪያውን ይግባኝዎን በጊዜው ለ RALS ካስገቡ ከችሎቱ በፊት መርማሪው መጀመሪያ ያነሱትን ጉዳዮች እንዲያሻሽሉ ወይም እንዲጨምሩ የመፍቀድ ስልጣን አለው። የመጀመሪያው የይግባኝ መግለጫ ለRALS በሰአቱ ካልደረሰ ግን መርማሪው ይግባኝዎን የመስማት ስልጣን *የለውም*። **ምንም ቢሆን RALS በመጨረሻው ቀን ይግባኝዎን መቀበሉን ያረጋግጡ!**

ይግባኝዎን በሰአቱ ማቅረብዎ ክስዎን ወደ ችሎት ሳይሄድ ከመፍታት አያግድዎትም። የRALSን ውሳኔ የመቃወም መብትዎን በቀላሉ ያስጠብቅሎታል። አንዴ የይግባኝ ቀነ ገደብ ካለፈ ግን የ RALS' ውሳኔ የመጨረሻና የማይለወጥ ውሳኔ ይሆናል።

## RALS የ ካውንቲውንም የሲያትልንም የመንጃ ፍቃድ ቢሽረውስ?

መርማሪው ከካውንቲ መንጃ ፍቅድ ጋር በተያያዘ ካለው የRALS ውሳኔ ውስጥ የተወሰኑት ላይ ነው ስልጣን ያለው። በሲያትል ውስጥ ለተሻረው መንገደኞችን የመጫን መንጃ ፍቃድ መቃወም ከፈለጉ ለሲያትል ይግባኝ ማለት ያስፈልግዎታል። የ RALS ውሳኔ የመጨረሻው ገጽ ስለ እነዚህ ሰፊ መረጃ ይዘረዝራል። የሲያትል የይግባኝ ጊዜ (10 ቀናት) ከካውንቲው ጊዜ (24 ቀናት) በጥዐም ያነሰ መሆኑን ይወቁ።

## ይግባኜ በሂደት ላይ እያለ መንዳት እችላለው?

ለቅጥር ፍቃድ/ለመንጃ ፍቃድ አዲስ አመልካች ከሆኑ ወይም ከአንድ አመት በላይ አገልግለው እረፍት ላይ የሆኑ ከዚህ በፊት የተፈቀደለት/መንጃ ፍቃድ ያሎት ሹፌር ከሆኑ መርማሪው ለክስዎ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ መንገደኛ መያዝ አይችሉም።

አሁን ላይ የተፈቀደልዎት/የመንጃ ፍቃድ የያዙ ከሆኑ እና RALS የእድሳት ማመልከቻዎን ከሻረው፣ወይም የማሽከርከር መብቶችዎን ካገደው/ከሰረዘው መርማሪው ይግባኝዎን በሚያገናዝብበት ጊዜ መንገደኞችን መያዝ መቀጠል ይችላሉ። አሁን ያልዎት (ጊዜያዊውን ጨምሮ) ፍቃድ/መንጃ ፍቃድ መርማሪው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የአገልግሎት ጊዜው ቢያልፍ ከRALS አዲስ(የተራዘመ)ጊዜያዊ ፍቃድ/መንጃ ፍቃድ ማግኘት አለብዎት።

## ሽምግልና ይቻላል?

ሽምግልና ሊኖር ይችላል። መጀመሪያ የመርማሪ ህግ Vን ያረጋግጡ (ሊንኩ መጨረሻ ላይ አለ)። ሽምግልና ለመጀመር ሂደቱ ላይ በቅድሚያ የተጻፈ ጥያቄ ያዘጋጁ።

## ከችሎቱ በፊት ምን መጠበቅ ይችላሉ?

በትንሹ ከችሎቱ ከሁለት ሳምንት በፊት መርማሪው ማሳሰቢያ ይልካል። ማሳሰቢያውን በጥንቃቄ ያንብቡ። የችሎቱን ቀን፣ሰአትና ፎርማት (ስልክ፣ቪዲዮ፣በአካል፣ወ.ዘ.ተ) ያዘጋጃል። ብዙ ጊዜ ለችሎቱ ስለጉዳዩ የመጀመሪያ ትርጓሜዎችና የመፍትሄ ሃሳቦችን ያካትታል። በይግባኝ መግላጫው ላይ ያነሱትን ሃሳቦች ለማሻሻልና ከችሎት በፊት የሚያስፈልግ ማንኛውንም መረጃ ለመላክ ቀነ ገደብ ያስቀምጣል።

ከችሎቱ ሁለት ሳምንት በፊት RALS ስለ ጉዳዮቹ የሚያብራራና RALS በችሎቱ ላይ እንደ ኤግዚቢት ማቅረብ የሚፈልገውን አብዛኛውን ወይም ሁሉንም ሰነድ የሚያሳይ ሪፖርት ለተለያዩ ተሳታፊዎች፣ፍላጎት ላላቸው ሰዎችና ለመርማሪው ያስገባል። ይህን በጥንቃቄ ያንብቡ።

በክሱ ላይ የRALS ፋይሎች የህዝብ መዝገቦች ናቸው፤ከችሎቱ በፊት ሁሉንም ፋይል መገምገም የሚፈልግ ሰው ከRALS ጋር ይህን ማዘጋጀት ይችላል (በኢሜይል pd.requests@kingcounty.gov ወይም በመደወል (206) 263-1977). ማንኛውም ሰው የመርማሪውን ሰነድም መጠየቅ ይችላል፤የመርማሪው መዝገቦች የሚገኙት ያለ ወጪ በኤሌክትሮኒካል መንገድ ነው።

## በዚህ የይግባኝ ሂደት ማን መሳተፍ ይችላል?

የስብሰባ ወይም ችሎት መርሃ ግብር ማዘጋጀት(እንደገና ማዘጋጀት)፣ቀነ ገደብ ማስቀመጥ፣ንቅናቄ ማዘጋጀትና መላሽ መስጠትና ምን አይነት ማስረጃ እንደሚወርብ፣ ምስክር እንደሚጠራ እና በችሎቱ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን መወሰን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ RALS እና ይግባኙን ያስገባው ሰው ብቻ መሳተፍ ነው የተለመደው።

ሌሎች በክሱ ላይ ፍላጎት ያላቸው ተሳታፊ ለመሆን የ"ጣልቃ ገቢ" ቦታ እንዲሰጣቸው ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህን ለመጠየቅ መርጃ ለማግኘት እባክዎ የመርማሪ ህግ X.Bን ይመርምሩ (ሊንኩ መጨረሻ ላይ አለ)። የጣልቃ ገቢነት ጥያቄዎች በአንዴ የሚሰጡ ሳይሆኑ ነገር ግን በተለያዩ ብዙ መስፈርቶች ይገመገማሉ።

## በይግባኝ ችሎት ላይ ምንድነው የሚፈጠረው?

### *የችሎቱ ሰአትና ፎርማት ምንድን ነው?*

መርማሪው የሚልከው ማሳሰቢያ የችሎቱን ቀን፣ሰአትና ፎርማት(ስልክ፣ቪዲዮ፣በአካል ወ.ዘ.ተ) ያዘጋጃል፤ይህን በጥንቃቄ ያንብቡ። የችሎቱ ፎርማት ምንም ቢሆን በሰአት ይገኙ ወይም ሙብትዎን አሳልፈው ሊሰጡ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ግን ቀድሞ የነበረው ችሎት ጭማሪ ሰአት ይጠቀምና ቀጣዩን ችሎት ያዘገየዋል፤ይህ ከተፈጠረ እባክዎን በትእግስት ይጠብቁ።

### *የተለመዱ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?*

እያንዳንዱ ክስ የተለያየ ቢሆንም በአጠቃላይ ግን አንዳንድ ነገሮች(ማመልከቻዎ ላይ ዋነኛ መረጃን መቀነስ፣ወይም መጠጥ ጠጥቶ ማሽከርከር ጋር የተያያዘ ወንጀል) *የግዴታ* ሽረትን ያስከትላል። ሌሎች ነገሮች (የጥቃት ወንጀል ወይም ብዙ ትናንሽ የተሽከርካሪ ጥሰቶችን የመሳሰሉ) ሽረትን ሊያስከትሉ ወይም ላያስከትሉ ይችላሉ።

### *የበፊት ወንጀልን ወይም ጥሰትን መከላከል እችላለው?*

አይቻልም።መርማሪው ፖሊስ ፣አቃቤ ህግ፣ተከሳሽ ወይም ፍርድ ቤት ባለፈ ክስ ላይ ያረጉትን እንደገና ግምት ውስጥ ማስገባት አይችልም። መዝገብዎ በሚለው ላይ ስለ ወንጀሉ ወይም ጥሰቱ *ማብራራት* ወይም *አውዱን* መግለጽ ይችላሉ እንጂ ወንጀል ወይም ጥሰት እንደሰራህ መከራከር አትችልም። ይልቁንም መርማሪው መዝገብዎና ማንኛውም አዲስ መረጃ ተሰጥቶት ይግባኝ በሚፈቀድበት ሁኔታ ላይ ይወስናል።

### *ችሎቱ እንዴት ነው የሚካሄደው?*

1. በይግባኝዎ ላይ ያነሱትን ጉዳዮችና ሃሳቦች በተመለከተ RALS ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ስላለበት RALS መጀመሪያ መናገር አለበት። RALS ምስክርነት ያቀርባል፤ በዋናነት ከችሎቱ ከሁለት ሳምንት በፊት RALS የላካቸውን ሰነዶቹን ብቻ ይሰጣል። ማስረጃን በመቀበል ረገድ ከፍርድ ቤቱ ይልቅ መርማሪዎች ያነሰ ችሎታ ቢኖራቸውም ለማንኛውም ሰነድ ተቃውሞ ማቅረብ ይችላሉ። ማንኛውንም ምስክር መጠየቅ ይችላሉ።
2. ከዛ ምስክርነት የማቅረብና ማንኛውንም ሰነዶች የምቅረብ ተራ የእርስዎ ነው፤ RALS ተቃውሞ ሊያነሳና ጥያቄዎች ሊጠይቅ ይችላል። RALS ያቀረቡትን ማንኛውም ምስክር ሊጠይቅ ይችላል።
3. በአካል ለሚደረግ ችሎት ማንኛውም ሰነድ ማቅረብ የሚፈልግ በትንሹ ሶስት ኮፒዎችን ማምጣት አለበት። (ለማንኛውም ከችሎቱ በፊት ላሉ ቀነ ገደቦች የተጻፈውን የመርማሪውን ማሳሰቢያ ያረጋግጡ።)
4. ከዚያ በኋላ እያንዳንዱ አካል ሌላው አካል አካል ላቀረበው ምላሽ የሚሰጥበት የተወሰነ ጊዜ አለው፤ቀጥሎም አጭር የመዝጊያ ንግግር ይኖራል።
5. በማንኛውም ሰአት መርማሪው ጥያቄ ሊጠይቅ ይችላል።
6. ሁሉም ምስክርነት በመሃላ መሆን አለበት ማለትም በእያንዳንዱ ምስክር መርማሪው ይምላል ማለት ነው።

### *እንዴት ኢድርጌ ክሱን በደንብ አቀርባለው?*

መርማሪው የላከውን ማሳሰቢያ በጥንቃቄ ያንብቡ። ውጤታም ምስክርነትና ሙግት እንዴት አንድ ልዩ ህግ በክስዎ ላይ እንደሚተገበር ይገልጻል። ገለጻዎች በማስታውሻ፣በጽሁፍ መግለጫዎች፣በፎቶግራፎች፣የጽሁፍ ማስረጃነት ያላቸው መዝገቦች እና በሚታዩ ነገሮች መልክ ሊሆን ይችላል።

በመሃላና በመስቀለኛ ጥያቄ(መጠየቅ) አልፎ በችሎቱ መካከል የሚቀርበው መግለጫ ነው በአጠቃላይ ግምት ውስጥ የሚገባ እሳቤ የሚሰጠው። ሁኔታውን ለመፍታት የሰሩትን ማንኛውም ስራ የሚገልጹ ሰነዶችና ምስክርነት ማቅረብ ይችላሉ።

### *ስለ ችሎት መዝገቦችስ?*

ችሎትዎ ይመዘገባል፤እና የመዝገቡንና የማንኛውንም ሰነድ ኮፒ መጠየቅ ይችላሉ። ምንም እንኳን የመርማሪው ቢሮ ብዙ መዝገቦችን በዲጂታል መንገድ ቢይዝም በተጠየቀው ውሂብ ብዛት መሰረት የማባዣ ወጪ ሊኖር ይችላል።

### ከችሎቱ በሁላ ምን ይሆናል?

ችሎቱ ከተዘጋ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ(የሳምንት መጨረሻ ቀናትና በአላትን ሳይጨምር ማለት ነው) በችሎቱ መዝገብ መሰረት የተገኙ እውነታዎችና ከነዚህ ግኝቶች የተገኘውን ድምዳሜ አካትቶ መርማሪው የመጨረሻ ውሳኔውን ይልካል። ሙሉውን ይግባኝ ሊቀበለው፣ሊሽረው ወይም ምካከል ላይ ያለ ነገር (ሁኔታዎችን ማሻሻል፣ቅጣቶችን መቀነስ ወ.ዘ.ተ.) ሊያረግ ይችላል።

የመርማሪው ውሣኔዎች እንዴት ይግባኝ እንደሚጠይቁ በሚያሳይ ጠቅላላ መረጃ ያልቃል። መርማሪው ከጽሁፍ መረጃ ውጪ ተጨማሪ መመሪያ መስጠት አይችልም። ይግባኝ ለማስገባት የሚያስፈልጉትን ትክክለኛ መስፈርቶች የመወሰንና የማሟላት ሃላፊነት የይግባኝ ባዩ ነው።

### ከመርማሪው ቢሮ ጋር ለመገናኘት ትክክለኛው መንገድ ምንድን ነው?

*መርማሪውን በስነ ስርኣታዊprocedural* qጥያቄዎች ማግኘት ቢችሉም ከጉዳዩ መሰረተ ሃሳብ ጋር ይተያያዙ መግለጫዎች ወይም ጥያቄዎች ግን መነሳትያለባቸው በስብሰባው ወይም በችሎቱ ወይም በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ለሁሉም አካል መቅረብ አለበት። የመርማሪው ሰራተኞች ከሁለቱም አካል ወደ መርማሪው ይተከለከለ ግንኙነት እንዳይኖር ደብዳቤዎችንና የስልክ ጥሪዎችን ያጣራሉ። በአጠቃላይ ኢሜይሎች መላክ ያለባቸው hearingexaminer@kingcounty.gov እና ኮፒ መደረግ ያለባቸው KCFHInspector@kingcounty.gov ።

### አግባብ ያለው ችሎት እንዳገኘው እንዴት መርማሪው ያረጋግጣል?

መርማሪዎች በRALS ላይ ጥገኛ ያልሆኑና ለRALS ወይም ሌላ ኤጀንሲ ልዩ አክብሮት የማይሰጡ ናቸው። መርማሪዎቹ የገንዘብ ፍላጎት ባላቸው፣ ቅድመ ፍርድ በሰጡባቸው ጉዳዮች ወይም ልሆነ አካል ባላቸው ግንኙነት ምክኛት አድሎ በሚያሳዩበት ጊዜ የይግባኝ ችሎቱ ላይ ላይሳተፉ ይችላሉ። አንድ ሰው መርማሪው ከመዝገቡ ውጪ ባለው ሁኒታ ተጽእኖ ያድርበታል ብሎ የሚያሳምን ምክኛታዊ መሰረት ካላቸው በአስቸኳይ ይሄንን ስጋት ወደ መረማሪው ትኩረት ማምጣት አለባቸው።

### ምን አይነት ህጎችና ደንቦች ናቸው በዋናነት ተግባራዊ የሚደረጉት?

የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን የሚገዙ ደንቦችን በተለይም KCC ምእራፎች 20.22 እና 6.64 እና የመርማሪው ህጎችን ማወቁ ብዙ ጊዜ ይረዳናል፤

- የኪንግ ካውንቲ ደንቦች፦ http://www.kingcounty.gov/council/legislation/kc_code.aspx
- የመርማሪው ህጎች፦ http://kingcounty.gov/independent/hearing-examiner/rules.aspx

መርማሪዎች ውሳኔያቸውን የሚሰጡት እነዚህን ምንጮች፣የህገመንግስቱ መርሆችና የፍርድ ቤቱን ውሳኔዎች መሰረት በምድረግ ነው።

በየአመቱ የነበሩ የመረማሪው ውሳኔዎችን ለማየት፦ https://kingcounty.gov/independent/hearing-examiner/case-digest/appeals/for-hire-enforcement.aspx

ከማንኛውም ጥያቄ ጋር ወደ መርማሪው ቢሮ መደወል ይችላሉ።

*Edited July 2023*